በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

*ሕዳር 18ቀን 2008 ዓ,ም*

## *<u>በርሃብ የሚቀጣ ጨካኝ ሥርዓት</u>*

*የሰው ልጅ በተፈጥሮ ያገኛቸውን መሬትን፣ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን ፣ ውሃን-----ለጥቅም ያውላቸዋል፤ ይንከባከባቸዋል። እነዚህን የተፈጥሮ ፀጋዎች በወጉ አለመጠቀም ግን ጉዳት ያደርሳል። ኢትዮጵያ በመልከዓ ምድር አቀማመጥና በአየር ንብረት ተስማሚነት የታደለች ነች። ይህን መልካም ገጽታዋን በሳይንስና ቴክኖሎጂ በመታገዝ በእንክብካቤ ይዞ የመጠቀሙ አካሄድ እምብዛም በመሆኑ የተፈጥሮ ሀብቷን የሰውን ኃይል ጭምር በሚያመረቃ ውጤት መጠቀም ስላልተቻለ ችጋር ደባላችን ሆኖ ዘመናት እየተቆጠሩ ነው።ሌላው ቀርቶ አንድ ምዕተ ዓመት በሚጠጋ ጊዜ 40% የነበረው ደን የለበሰ ምድራችን ተራቁቶ አሁን 4% እንኳ መኖሩ ያጠራጥራል። የመሬታችን መራቆትና የዓለም አቀፉም የአየር ንብረት መዛባት ጋር በተያያዘ በየአስር ዓመቱ የሚከሰተው ድርቅ በ100 ሺዎች ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን ህልፈት ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። በቅርቡ ደግሞ በየአስር ዓመት የሚከሰተው ድርቅ ዑደቱን በየሦስትና አራት ዓመታት እያሳጠረው እንደሆነ ይነገራል።*

*ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የተፈጥሮ ችግር እንዳለ ሆኖ ሰው ሰራሹ ችግርም ችግራችንን የሚያግዝፍ ክስተት ለመሆኑ አሌ አይባልም። ካለፉት መንግሥታት ለየት ባለ ሁኔታ ለችግሮቻችን መደራረብ ፣ ለሕዝባችን መራብ ፣---- አሁን ያለው ጨካኝና አምባገነን የወያኔ ሥርዓት ዋነኛ ተጠያቂ ነው። ወያኔ ጨካኝ፣ ፋሽስት ፣ በዘር መድሎ አምላኪ ከመሆኑም በላይ ለበቀለበት ሕዝብ እንኳ ርኅራሄ ያልነበረው እንደነበር በ1976 ዓ.ም (1984 እ.አ.አ) በድርቅ ለተጎዳው የትግራይ ህዝብ ከውጪ አገር የተገኘውን እህልና ቁሳቁስ መልሶ ለተለያዩ አገሮች በእጅ አዙር ሺጦ ለመሳሪያ መግዣና ለሠራዊቱ ቀለብ ማዋሉን በሰነድና በቀድሞ አባላቱ ወቅቱን ጠብቆ ተጋልጧል። ባጠቃላይ ከርሃብና ቸነፈር አትራፊ ድርጅት ነው። የአገርና የሕዝብ ጠላት ነው።*

*ወያኔ ወደ መሐል አገር ሲገሰግስ ለጥፋት ባሰማሩት ኃያላን እየታገዘ የኢትዮጵያን ሠራዊት አስወግዶ አገሪቱን በጠመንጃ ኃይል ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የከፋት የተፈጥሮ ባሕርዩ እየባሰበት መጥቷል።ገና ከመነሻው 80 ሺህ የሚሆኑ የመንገድ ሥራ ድርጅት ሠራተኞችን በትኖ ለርሃብ፣ ለእርዛት፣ ለበሽታና ለሞት አጋለጠ። ቀጥሎ የሕንፃ ስራ ድርጅት በ10ሺዎች የሚቆጠሩ እንዲሁ አውላላ ሜዳ ጣለ። የባህር ትራንዚት ሠራተኞችም የዚሁ የወያኔ/ኢህአዴግ የግፍና ጭካኔ ሰለባ ሆነው ለሦስት ወራት መስቀል አደባባይ ( አብዮት አደባባይ) ድንኳን ጥለው ፍትሕ ለማግኘት ሲጠባበቁ በታጣቂ ተደብድበው፣ ተቀጥቅጠው ፣ በጫማም ተርግጠው ተባረሩ። የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊትም በዓለም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተበትኖ ለልመና ጎዳና ላይ ተሰማርቶ አይተን አእምሮአችን ደማ።*

*ይህ በእንዲህ እንዳለ በውስጥ ጉዳያቸው ጣልቃ በመግባቱና ከላይ የጠቀስናቸውን ግፎችም በመመልከት የባንክና ኢንሹራንስ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ጀመሩ። የአጋሚዶው ቡድን ምላሹ በምትካቸው ሌሎች አመልካቾችን መቅጠር እንደሚሆን ማስታወቂያ ሲያወጣ ሙያዉን የሚመጥኑም የማይመጥኑም የወያኔ ማህይም ካድሬዎችም ጭምር ለመቀጠር ሲያመለክቱ ዙሪያ ጥምጥም ተሰልፈው ሲጠባበቁ ያዩ ወገኖቻችን ትዝብታቸውን በየአጋጣሚው ሲገልጹ ቆዩ፤ያንዱ ሞት ለሌላው ልደት ማለት ይህ ይሆን? በጣም አሳፋሪ ድርጊት ነበር።*

*ወያኔ ይህ ክስተት የእኛን አቋም የሚለካበት መሳሪያ ሆነውና ቀጣይ የግፍ ተግባሩን አጠናከረ።በሲቪል መስሪያ ቤቶች የራሱን ካድሬዎች ለመተካት ሲባል ልምድ ያካበቱና የትምህርት ደረጃቸው ከፍተኛ የሆኑና ዕውቅና ያላቸውን ሠራተኞች በማሰወገድ ዕውቀቱም ልምዱም የሌላቸውን በመሰግሰግ ያለአማራጭ ያባረራቸው የትእየለሌ ናቸው። ከመባረር የተረፈውና አዲስ ለመቀጠር የወያኔን መስፈርት ያመለጠ ሠራተኛ በካድሬ ወከባ በነፃ ሕሊና ሰርቶ ምርታማ መሆኑ ቀርቶ በየዕለቱ ከሚንረው የዋጋ ውድነት ጋር የሚመጥን ደመወዝ ካለማግኘቱም በላይ የማያባራ መዋጮ ቀፍድዶት ቤተሰቡን መግቦ መኖር አቅቶታል። ሕዝባችን በቀን ሦስት ጊዜ ምግብ ማግኘት የሚችልበት ፌዝ ሆኖ በ24 ሰዓት አንዴ ለመመገብ የቤተሰብ አባላት ተራ ለመጠባበቅ እንደተገደደ ዘወትር የምንሰማው አሳዛኝ መርዶ (ዜና) ነው።መቼም ህዝብ ብሶቱን የሚገልጽባቸው አባባሎች ብዙ ናቸው። ይህን በየዕለቱ ምግብ የማግኘት ፍዳ ሲገልጽ "**ቁምሳ**" ብሎታል።*

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*ቁርስና ምሳ አንድጋ( አንድ ጊዜ) በልቶ ያለ እራት ውሎ ማደርን ያመለክታል። ያውም ቢሆን ሲገኝ ሲታጣ ነው። በት/ቤቶች ሕፃናት በጠኔ እየወደቁ መታየታቸው ሌላው በቂ ማስረጃ ነው። ለጥጋበኞቹ የወያኔ ባለሥልጣናትና ለደጋፊዎቻቸው ግን ብሶትና ችግር አይታቸውም፤ ቢታያቸውም ፣ ቢያውቁትም ደንታ የላቸውም።ሌላው ቀርቶ በቁጥጥሩ ስር ያሉ እስረኞች ምግብ እንዳይገባላቸው መከልከሉን፣ ቢገባም ቀንሱ ማለቱ ተሰምቷል።*

*በውሸት ፣ በፕርፖጋንዳ፣ በማታለል፣ በዘረፋ__ የተካነው ወያኔ/ኢህአዴግ ኢኮኖሚው ግብርና መርነው፣ ገበሬው ኢህአዴግን ይደግፋል እያለ የሚሸነግለውን ገበሬ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር በሙስና በመሞዳሞድ ለየአካባቢው መሬት ተስማሚነቱ በምርምር ያልተደገፈ ማዳበሪያ ማራገፊያ ስላደረገው ማሳዎቹ ስለመከኑ ዕዳ ተሸካሚ ሆኖ መክፈል ባለመቻሉ ጥማድ በሬዎቹን ያለዚያም የቤት ከዳን ቆርቆሮዎቹን እንዲሸጥና እንዲከፍል መገደዱ የተረጋገጠ ነው። በዚሁ ላይ በአገሪቱ አብዮት አስነስቶ የዘውዱን ሥርዓት እንዲወድቅ ያደረገው ሕዝባዊ መፈክር “ መሬት ለአራሹ” ውሉን ስቶ ቀደም ሲል መሬት በወታደራዊ ደርግ ቁጥጥር አሁን ደግሞ በወያኔ/ኢህአዴግ እጅ ገባ። ገበሬው የራሴ የሚለው መሬት ባለመኖሩ ይዞታውን በወጉ የመንከባከብና የመጠበቅ መብቱን ተገፎ የወያኔ ጥገኛና ጭሰኛ በመደረጉ የተረጋጋ የግብርና ሥራ ሊያካናውንና ምርቱን ሊያሳድግ የሚችልበት አጋጣሚና ዕድል ጨልሞ ቤተሰቡን የሚመግብበትና ለገበያ የሚያቀርበው ትርፍ ምርት የለም።*

*ብዙ ጊዜ እንደሚለፈፈው ግብርና ኢኮኖሚውን ሊመራ ቀርቶ ሊያግዝ እንኳ የሚችል አልሆነም።የገበሬውን አኗኗር ለመለወጥ የመስኖ ውሃ መጥለፍ ፣ በቁፋሮ ውሃ ማውጣት ፣ የእህል ዘር ጥራትን መጠበቅ፣ የእርሻ ዘዴውን ዘመናዊ ማድረግ፣ -----የመሳሰሉትን ለመከወን የሚያስችል በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ከአበዳሪና ለጋሽ መንግሥታት /ድርጅቶች የጎረፈለት ወያኔ ገንዘቡን ኪሱ ከቶ 25 ዓመታትን ያሳለፈው በባዶ ፕሮፖጋንዳ ላይ ተጠምዶ ስለነበር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለረሃብ ተጋለጡ።*

*የሚገርመው፣ የሚያሳዝነውና የሚያስቆጨው ጉዳይ የርሃቡ ስፋት የሚሊዮኖችን ሕይወት ሊቀጥፍ እንደሚችል የውጪ ሚዲያዎችና የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ ሌሎች ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ስጋታቸውን ለዓለም ሕብረሰብ እያሳወቁ ባሉበትና አደጋውን ለመቋቋም በሚንቀሳቀሱበት ፣ አንዳንድ የእርዳታ ድርጅቶች በአገሪቱ በተለያዩ መስኮች ለእርዳታ ያቀዱትን በጀት አጥፈው ረሃቡን ለመቋቋም ወስነው እያለ ፣ ወያኔ/ኢህአዴግ የረሃቡን ክስተት ለመደበቅ ደፋ ቀና ሲል መታየቱ ነው። ይህን በዜጎች ህይወት ላይ ያንዣበበውን ርሃብና እልቂት ለመደበቅ የታሰበው ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው ከወራት በፊት አገሪቱ በምግብ ራሷን መቻሏ ፣በቂ ምርት መመረቱንና ከእርዳታ ጥገኝነት መላቀቋን ለይስሙላው ፓርላማ ሪፖርት ካደረጉ ብዙም ሳይሰነብት ስለነበር የዓለም አቀፉን ህብረሰብ በተለይም ለጋሾቹንና አበዳሪዎቹን ለማሞኘት የታሰበ ማስተባበያ ነበር። አቶ ቴዎድሮስ አድኃኖም በበኩላቸው ከ90 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ 8 ሚሊዮን ቢራቡ ምንም አይደል በማለት ተሳልቀዋል። በመሆኑም ሥርዓቱ ሕዝብን በርሃብ የሚቀጣ ጨካኝ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ ነው። ሁኔታው ዓይን ያወጣ ቅጥፈት ለመሆኑ የተለያዩ ታላላቅ የሚዲያ ተቋማት እና( ቢቢሲ (BBC)) የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ጨምሮ የችግሩን መባባስ በተዳጋጋሚ እየዘገቡ ስለሆነ ሥርዓቱ አርቃኑን እንዲቀር ሆኗል።ርሃብ ጊዜ አይሰጥም፤ ለተራብ የማይራራ አንጀት የወያኔና የአጫፋሪዎቹ በመሆኑ ሕዝብ እየተራበ በመቶ ሚሊዮን ብር ረሃብተኛ በግድ እያዋጣ ለገዢዎች በዓል የአስረሸ ምቺው ማድመቂያ እንዲሰጥ ይገደዳል( የብአዴንን 35 ዓመት ምስረታ በዓልንና ሌሎች የወያኔ በዓሎችን ይጠቅሷዋል) እነዚህ የፋሽስትና የናዚ ደቀ መዝሙሮች ለአምባገንና ጨቋኝ አባሎቻቸው መኖሪያ ቤትና ለአንድ ባለሥልጣን 25 ሚሊዮን የሚያወጣ የተሟላ ቪላ ቤት፣ ለ6 አባሎቻቸው ባጠቃላይ ከ150 ሚሊዮን ብር የማያንስ ውጪ በማድረግ ቤት ለማሳራት ማቀዳቸውን ያለሐፍረት በአደባባይ ይናገራሉ።ባላቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ይሏል እንዲህ ነው።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ሥርዓት የሚደርስበት ግፍና ሰቆቃ በፋሽስትም ፣ በናዚም ደርሶ ከታየው የሚስተካከል ነው።የዘመኑ ግጥምጥሞሽ ደግሞ መከራችንን አራዝሞታል።ምዕራባውያን በአፍሪካ ቀንድ ባላቸው ስትራቴጂያዊ ጥቅም ይህን ግፈኛ ሥርዓት እየረዱ ሕዝቡን ያለዕዳው ዋጋ እንዲከፍል ፈርደውበታል። ይህ እንዳለም ሆኖ ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም ነውና ለራሳችን ነፃነት የሚያስከፍለውን ማንኛውንም መስዋዕትነት ከፍለን አገራችንን ፣ ተተኪውን ትውልድ ነፃ ካላወጣን በተማጽኖ ነፃ መውጣታችን ዘበት ነው።ከሞኝ ደጅ ሞፋር ይቆረጣል እንዲሉ አገር ሲቆረስ ፣ ለም መሬታችን ለባዕዳን ሲሰጥና ሲቸበቸብ፣ አንጡራ ሐብታችን ወደ ውጪ አገር ሲሻገር፣ ለመብት የሚከራከሩና ለዕውነት የቆሙ በእስር ሲመቅቁ ፣ ማሰቃየት ፣መግደልና መሰወር ሲዘወተር፣ በብልሹ ሥርዓት ሳቢያ ሚሊዮኖች ለረሃብ ሲጋለጡ ከመታገል መቦዘን አንድም ወር ተራን ጠብቆ በዚሁ የግፍ አዙሪት መውደቅ፣አለያም የዜግነትን ግዴታ ባለመወጣት የታሪክ ተጠያቂ መሆን ነው ትርፉ።*

*የወያኔን የግፍና የጭካኔ አገዛዝ ቀጣይነት ከፈቀድን ባርነትን የተቀበልን እንደሆነ እንገንዘብ፤ ባርነት፣ ተገዢነትና ተንበርካኪነት የወረስነው ታሪክም ባሕልም አይደለም። ለተተኪው ትውልድም ይህን የታሪክ ጭቅቅት ልናቀብለው ቢያንስ ሰብአዊ ፍጡሮች መሆናችን ያስወቅሰናል፣ ይከለክላል።ብዙ ጊዜ እንዳሳሰብነው በሙያቸው እና ከሕበረተሰቡ ጋር ማለትም ከተማሪዎች ፣ ከወላጆች ----ባላቸው መስተጋብር መምህራን ሕዝብን ለመቅረብና ለማስተባበር ባላቸው ርቱዕ ሚና ትግሉን በግምባር ቀደም እንዲመሩ በድጋሚ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ አጥብቆ ያሳስባል።ተማሪዎች ፣ ወላጆች፣ የፋብሪካና የመንግሥት ሠራተኞች ፣የንግዱ ማህበረተሰብ፣ ገበሬው፣----ከርሃብ ከጭቆና ፣ ከስደት ---ለመላቀቅ አንዲሁም በረሃብ ለተጎዱ ወገኖቻችን በሚደረገው ሁለንተናዊ ድጋፍና እርዳታ ከመንቀሳቀስ ጎን ወያኔን በማሰወገድ በሕዝብ የተመረጠ ሥርዓት እንዲቋቋም ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪያችንን እናስተላፋለን።*

*ርሃብ የብልሹ ሥርዓት ውጤት ነው!!*
*የሕዝብ ሰቆቃ ያብቃ!!*
*በእምቢተኝነት የሚንቀሳቀሱትን እንደግፍ!!*
*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!*